# በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ
# አጠቃቀም ላይ
# ለሚቀርቡ ጥቆማዎች
# ወሮታ ስለሚከፈልበት ሁኔታ
# የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ነሐሴ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ
# ለሚቀርቡ ጥቆማዎች ወሮታ ስለሚከፈልበት ሁኔታ
# የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2001

በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ መጠቀም ሲገባቸው በማይጠቀሙ ወይም መሣሪያውን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ጥቅም ላይ የሚያውሉትን በተመለከተ ተጨባጭ መረጃ ለሚያቀረቡ ጠቋሚዎች በመንግስት የሚፈቀድ አበል እንደሚሰጥ የተገለፀውን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 22 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የአፈጻፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ ለሚቀርቡ ጥቆማዎች ወሮታ ስለሚከፈልበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2001 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. **"የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ"** ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ማለት ነው፡፡
2. **"ደንብ"** ማለት በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 ነው፡፡
3. **"መመሪያ"** ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በሚመለከት በገቢዎች ሚኒስቴር የወጣ መመሪያ ቁጥር 46/1999 ነው፡፡
4. **"ጠቋሚ"** ማለት በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ባለመጠቀም ወይም አጠቃቀም ላይ የሚፈፀሙ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ለባለሥልጣኑ የሚጠቁም ማንኛውም ሰው ሲሆን የባለሥልጣኑን ሠራተኛ አይጨምርም፡፡
5. **"ተጨባጭ መረጃ"** ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሆኖ መሣሪያውን ባለመጠቀም ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ በመጠቀም

የሚካሄድን የንግድ ሥራ በሚመለከት ለባለስልጣኑ የቀረበ እና ትክክለኛነቱ በማስረጃ የተረጋገጠ መረጃ ነው፡፡

6. **"ተደጋጋሚ መረጃ"** ማለት በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ላይ በተመሳሳይ ወይም በተለያዩ የጥፋት ዓይነቶች በተለያዩ ቀናት መፈፀማቸውን የሚያመለክት በማስረጃ ተደግፎ የሚቀርብ ጥቆማ ነው፡፡
7. **"መረጃ ተቀባይ"** ማለት በጠቋሚ የሚቀርቡ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ተቀብሎ ለዚሁ በተዘጋጀ የተለየ መዝገብ ላይ በመመዝገብ ለጠቋሚው በማስረጃነት የሚያገለግል ካርድ ወይም መለያ ኮድ የሚሰጥ በባለሥልጣኑ የተመደበ ሠራተኛ ነው፡፡
8. **"ለማስረጃነት የሚያለግል ካርድ"** ማለት ጠቋሚው ባቀረበው ጥቆማ የተፈፀመውን ጥፋት ዓይነት፣ ቀን፣ ሰዓት፣ የመሣሪያውን ተጠቃሚ ስም ወይም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የጠቋሚውን ስም ወይም መለያ ኮድ የያዘ ጠቋሚው ጥቆማውን ስለማቅረቡ በማስረጃነት እንዲያገለግለው የሚሰጠው ማረጋገጫ ነው፡፡
9. **"መለያ ኮድ"** ማለት የመረጃውን ሚስጥራዊነት እና የጠቋሚውን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ጠቋሚውና ባለስልጣኑ ብቻ የሚገናኙበት ለጠቋሚው የሚሰጥ መለያ የሚስጥር ቁጥር ነው፡፡
10. **"ማሽን ለመፍታት ሙከራ ማድረግ"** ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ያለአገልግሎት ማእከሉና ያለባለሥልጣኑ እውቅና ለመፍታት፣ ወይም ለመግጠም፣ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽኑ ሳይበላሽ እሽጉን ለማንሳት፣ ወይም አካሉን ለመቀየር መሞከር፣ ወይም እንዚህን የመሳሰሉ አድራጐቶች መፈፀም ነው፡፡
11. **"የአገልግሎት ማዕከል"** ማለት በመመሪያው አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (4) ላይ የተሰጠው ትርጉም ነው፡፡
12. **"ወሮታ"** ማለት በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ተጨባጭ መረጃ ለሚያቀርብ ማንኛውም ሰው የመረጃው ትክክለኛነት በባለስልጣኑ ከተረጋገጠ በኂላ በገንዘብ የሚሰጥ ክፍያ ነው፡፡
13. **"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

14. "ዋና ዳይሬክተር" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

## 3. መረጃዎችን ስለማቅረብ

1) ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው ወይም ድርጅት መሣሪያውን ባለመጠቀም ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ በመጠቀም የሚያካሂደውን ማናቸውንም ሕገ ወጥ ተግባር የሚመለከቱ መረጃዎችን ጥፋቱ በተፈፀመ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ:-

   ሀ. በታክስ ባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት በመቅረብ፣ ወይም

   ለ. ስልክ በመደወል፣ ወይም

   ሐ. በፖስታ ወይም በፋክስ ወይም ኢ-ሜይል በመጠቀም፣

 ጥቆማ መስጠት ይቻላል፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መረጃ በመስጠት ትብብር እና ድጋፍ ያደረጉ በሙሉ በዚሁ መመሪያ መሠረት የአበል ክፍያ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል፡፡

## 4. የመረጃ ተቀባይ ኃላፊነት

1. የባለስልጣኑ የመረጃ ተቀባይ ሠራተኛ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 3 የተመለከቱት መረጃዎች ሲቀርቡለት ለዚሁ በተዘጋጀው መዝገብ ወይም የኮምፒውተር ሥርዓት:-

   ሀ. መረጃው የቀረበበትን ቀንና ሰዓት፣

   ለ. መረጃው የሚመለከተውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበትን ሰው ስም፣ የንግድ አድራሻና ሌሎች ተጨማሪ መለያ ምልክቶች፣

   ሐ. የተፈፀመውን ሕገ ወጥ ድርጊት ዓይነት በዝርዝር፣

   መ. የተጠቀሰው መረጃ በተደጋጋሚ የቀረበ ከሆነ የቀረበበትን ተራ፣ ለስንተኛ ጊዜ እንደቀረበ፣

   ሠ. የመረጃ አቅራቢውን ፈቃደኝነት በመጠየቅ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥርና የቤት ቁጥር፣ በአግባቡ ይመዘግባል፡፡

ፈ. መረጃው ቀደም ብሎ በሌላ ሰው የቀረበ ከሆነ ይህንኑ ለአዲሱ መረጃ አቅራቢ ይገልፃል፡፡

2. ለመረጃ አቅራቢው በማስረጃነት የሚያገለግል የመረጃ ተቀባዩን ስም፣ የሥራ ድርሻና ፊርማ የያዘና የባለስልጣኑ ማኅተም ያለበት ካርድ ይሰጠዋል፡፡
3. መረጃ አቅራቢው መረጃውን የሰጠው ስልክ በመደወል ከሆነ መረጃ ተቀባዩ መረጃው የቀረበበትን ቀንና ሰዓት፣ ጥቆማ የቀረበበትን ሰው ስም፣ የተፈፀመውን ሕገ ወጥ ድርጊትና እንዲሁም መረጃው የቀረበበትን ተራ ቁጥር ለመረጃ አቅራቢው በመንገር በማስረጃነት የሚያገለግል ካርድ በ48 ሰዓት ውስጥ ቀርቦ መውሰድ የሚገባው መሆኑን ይገልጽለታል፡፡
4. መረጃ ተቀባዩ የተቀበለውን መረጃ ሚስጥራዊነቱን በጠበቀ ሁኔታ ለመረጃ አቅራቢው በማስረጃነት የሚያገለግል ካርድ የተሰጠው መሆኑን ጭምር በመግለጽ ለሚመለከተው ኃላፊ መረጃውን እንደተቀበለ በ30 ደቂቃ ውስጥ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
5. የጠቋሚውን ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይጥልና የመረጃ ብክነት እንዳይኖር የባለስልጣኑ መረጃ ተቀባይ በጥቆማ የተገኘውን መረጃ የጠቋሚውን ማንነት ለመለየት የሚያስችል ምስጢራዊ መለያ /ኮድ/ በመስጠት መረጃውን በከፍተኛ ጥንቃቄ የመጠበቅ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡

## 5. <u>ለመረጃ አቅራቢ ወሮታ ስለሚሰጥበት ሁኔታ</u>

1. ለመረጃ አቅራቢ የሚሰጠውን አበል ለማግኘት የቀረበው መረጃ ተጨባጭ የሆነና ትክክለኛነቱ በባለሥልጣኑ የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡
2. አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የሆኑ መረጃዎች ከቀረቡ መረጃው ቀደም ብሎ በሌላ ሰው የቀረበና የተመዘገበ መሆኑን በኋላ ለመጣው መረጃ አቅራቢ በመግለጽ ወሮታው መረጃውን በመጀመሪያ አቅርቦ ላስመዘገበ ሰው ይሰጣል፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም መረጃው የተሰጠው ከአንድ በላይ በሆኑ ጠቋሚዎች በአንድ ላይ በጋራ በግንባር በመቅረብ በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ላይ የተመለከተው ሽልማት ለጠቋሚዎቹ እኩል ይከፋፈላል፡፡

## 6. ለመረጃ አቅራቢ የሚሰጥ የወሮታ መጠን

1) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው ወይም ድርጅት መሣሪያውን ባለመጠቀም ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ በመጠቀም የሚያካሂደውን ሕገ ወጥ ድርጊት የሚመለከቱ ተጨባጭ መረጃዎች በተለያዩ ሰዎች በቀረቡ ጊዜ የመረጃው ትክክለኛነት በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ በተፋጠነ የወንጀል ፍርድ ሂደት (RTD) ሊያስከስስና ሊያስቀጣ የሚችል መሆኑ ሲታመንበት ወዲያውኑ በሚከተለው መጠን ለጠቋሚው ወሮታ ይከፈላል፡፡-

   ሀ. መረጃው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ገዝቶ አለመጠቀምን ወይም በሥራ ላይ አለማዋልን የሚመለከት ሲሆን ብር 1,250 /አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/

   ለ. መረጃው ተገቢ ባልሆነ መንገድ መሣሪያውን ስለመጠቀም ማለትም የእጅ በእጅ ሽያጭ ወይም ህገ ወጥ ደረሰኝ፣ ወይም ሕጋዊ ቢሆንም መሣሪያው እየሠራ ማንኛውንም ሌላ ደረሰኝ መጠቀም፣ ደረሰኞችን ደጋግሞ መጠቀም የመሳሰሉትን የሚመለከት ሲሆን፣ ብር 2,500 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/

   ሐ. የመሣሪያውን እሽግ የፈታን ወይም ለመፍታት የሞከረን ለሚጠቁምና ተጨባጭ ማስረጃ ላቀረበ ብር 5,000 /አምስት ሺህ ብር/

   መ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እና (ለ) የተመለከቱት ጥፋቶች በአንድ ጊዜ መፈፀማቸውን ለሚጠቁም በየጥፋቶቹ ዓይነት የተመለከተው ወሮታ ይከፈለዋል፡፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም "በተፋጠነ የወንጀል ፍርድ ሂደት ሊያስከስስና ሊያስቀጣ የሚችል መሆኑ ሲታመንበት" ማለት ጥቆማው እንደቀረበ ለወንጀል መርማሪ ተመርቶ በእለቱ ከተጣራ በኋላ የምርመራ መዝገቡ ለዐቃቤ ሕግ ሲቀርብና ክስ ቢመሠረት ማስቀጣት የሚችል መሆኑ በዐቃቤ ሕጉ ሲረጋገጥ እና በፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሰጥበት ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የወሮታ ክፍያ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀረበው ጥቆማ መነሻ በተፈፀመው ጥፋት በባለሥልጣኑ ከሚጣለውና ከሚሰበሰበው አስተዳደራዊ መቀጫ ላይ 50% /ሃምሣ በመቶ/ በመንግሥት ከሚፈቀደው በጀት ለጠቋሚው ይከፈለዋል፡፡

4) የመረጃ አቅራቢውን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ሲባል የአበል ክፍያ እስኪፈጸም ድረስ የመረጃው አቅራቢ ማንነት በተለየ ሁኔታ በሚዘጋጅ መለያ (ኮድ) በሰነድ ይያዛል፡፡

5) መረጃ አቅራቢው አበል የሚያስገኝለትን መረጃ ያቀረበው ለተደጋጋሚ ጊዜ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ወይም (ለ) ወይም (ሐ) ከተመለከተው የአበል መጠን በተጨማሪ ከ5% -10% /ከአምስት እስከ አስር በመቶ/ ታክሎበት አበሉ ይሰጠዋል፡፡

6) በተደጋጋሚ ለተሰጡ መረጃዎች ከሚሰጠው አበል ተጨማሪ ሆኖ የሚከፈለው ክፍያ፡-

   ሀ) ለ2ኛ ጊዜ ለተሰጠ መረጃ የአበሉን 5% /ከመቶ አምስት/፣

   ለ) ለ3ኛ ጊዜ ለተሰጠ መረጃ የአበሉን 7% /ከመቶ ሰባት/፣

   ሐ) ለ4ኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ በተደጋጋሚ ለተሰጠ መረጃ የአበሉን 10% /ከመቶ አስር/፣

   ይሆናል፡፡

## 7. ለወሮታ ክፍያ ስለሚውለው ገንዘብ

ለመረጃ አቅራቢ የሚከፈለው አበል ከመንግስት በሚፈቀድ በጀት ይሸፈናል፡፡

## 8. በጥቆማ ላይ ገደብ ስለማድረግ

በአንድ ሰው ተመሣሣይ ጥፋት በተለያየ ጊዜ ተደጋግሞ በመፈፀሙ ምክንያት በሚቀርብ ጥቆማ ለ3 ሰዎች የወሮታ አበል ከተከፈለ ጥቆማ የቀረበበት ሰው ተከሶ እስኪፈረድበት ድረስ በተመሳሳይ ጥፋት በሌላ ሰው የሚቀርብ ጥቆማን ባለሥልጣኑ ላይቀበል ይችላል፡፡

## 9. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ_________ ቀን 2001 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር